# የዶር ብርሃኑ ፀረ አንድነት የትብብር ቅድመ ሁኔታና ‘አዲሱ’ የኦነግ ሬፈረንደም

***“ Those who call themselves as ‘unity forces’ should reconsider and investigate their positions and abandon putting unity as a precondition for coalition building in order to bring them to the fold. ...... We should move from competition to coalition and collaboration.”***

Dr Berhanu Nega, March 2012

***1.3. To facilitate the rights of self determination of the Oromo people, other peoples and individuals in Ethiopia***

***በ January 1, 2012 ከታወጀው ‘አዲሱ’ የኦነግ ፕሮግራም***

ከላይ በመግቢያው የተጠቀሰውና የዚህ መልእክት መነሻ የሆነው ዶር ብርሃኑ በቅርቡ የድርጅታቸውንና የኦነግን ጣምራ ዘመቻ አስመልክቶ ከሰጡት የማጠቃለያ ንግግር የተቀነጨበ ሲሆን ሁለተኛው ከ ‘አዲሱ’ የኦነግ ፕሮግራም የተወሰደ ነው። በሁለቱ ሃሳቦች መሀል ያለውን ዝምድናና ተደጋጋፊነት ለማየት እንሞክራለ።

መግለጫው ግልፅ በሆነ ሁኔታ እንዳስቀመጠው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ድርጅት ከኦነግ ጋር ለመተባበር ከፈለገ የኢትዮጵያን አንድነት ጥያቄ ውስጥ ማስገባት አለበት። በሌላ አባባል ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ከኦነግ ጋር ለመተባበር የኢትዮጵያን አንድነት እንደ ትብብር ቅድመ ሁኔታ ማቅረብ የለባቸውም።

ትብብር የጋራ አላማን ለማሳካት ከአንድ በላይ በሆኑ ድርጅቶች መካከል በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የሚመሰረት ስልታዊ የፖለቲካ መሳሪያ ነው። ‘ትብብር’ በራሱ ግብ ሳይሆን ወደ ግብ የሚያደርስ መንገድ ነው። ትብብር ጥረቶችን በማስተባበር አቅምን ከማጎልበቱም በላይ ባንድ ድምፅ መናገርም የማስቻል ጠቀሜታ አለው። እያንዳንዱ ትብብር እንደየሀገሩ ፖለቲካዊና ነባራዊ ሁኔታዎች የየራሱ ቅርፅና ይዘት ቢኖረውም ማንኛውም ትብብር መለያ የሆኑ የወል ባህርያት አሉት። ከትብብር ባህርያት ዋነኛው መርህን የተመረኮዘ መሆኑ ሲሆን ትብብር የቱንም ያህል ሊጠቅም ቢችል ከመሰረታዊ አላማ (ፕሪንሲፕል) ጋር በምንም መልኩ የሚጋጭና መርህን ለትብብር የሚሰዋ መሆን የለበትም። ከህዝባችን ፀረ ዘርኝነትና ሀገርን ከበታኞች የማዳን ትግል አኳያ ‘አላማ’ የምንለው ባጠቃላይ መልኩ ኢትዮጵያና ህዝቧን ማለት መሆኑን ከወዲሁ ማሳወቁ ተገቢ ይሆናል። በታሪክ አያሌ የትብብር ታሪኮችን አይተናል። ከመለስተኛ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ አጀንዳ ማስፈፀሚያነት አንስቶ ሀገር ማዳንን የሚያህል ዋጋ ያለው የህብረት ምሥረታ። በሀገራችን የተቃውሞ ትግል ታሪክ ውስጥ ባለፉት ህያ አመታት ቢያንስ ሁለት አበይት የፖለቲካ ስብስቦችን አይተናል ኢድሀቅና ኢዴሀህ ተጠቃሽ ናቸው። ሁሉንም የወል የሚያደርጋቸው ምናልባትም ካሁኑ የኦነጉ ዶር ብርሃኑ ‘ቅድመ ሁኔታ’ የሚለያቸው ጉዳይ ህብረቶቹን ለመፍጠር ኢትዮጵያዊነትን ጥያቄ ውስጥ ያለማስገባታቸው ነው።

ለመሆኑ ዶር ብርሃኑ ለምን ኢትዮጵያዊነት የትብብር ቅድመ ሁኔታ እንዳይሆን ፈለጉ? ነፃ ላወጣው ነው የሚሉትን ኢዮጵያዊነት ዛሬ ስሙ እንዳይነሳ ከፈለጉ አራት ኪሎ ሲገቡ ሊያከብሩት ነው? እውን ኢትዮጵያን ለማዳን ኢትዮጵያዊነትን መካድ ጤነኛ የፖለቲካ መስመር ነው?

ህዝባችን ላያሌ አመታት ከአፄ ሀ/ሥላሴ ጉልታዊ ሥርአት ጀምሮ እስከ ፋሺስታዊው ደርግ ለኤኮኖሚያዊ ፍትህና ለሙብት መከበር ታላቅ ተጋድሎ አካሂዷል ይሁን እንጂ ይህ የትግል ሂደት ግቡን ሳይመታ አሁን ሥልጣን በጨበጠው ዘረኛ ቡድን ተሰናክሏል የግፍ ግፍ እንዲሉ ይኸው ዘረኛ ሥርአት ቋንቋን ያማከለ ከፋፋይ የዘር ክልል ከመመሥረቱ በላይ ከህዝቡ ፍላጎት ውጭ 'የራስን ዕድል በራስ መወሰን' በሚል ሽፋን ጠመንጃ በተደገነበት 'ሪፈረንደም' የሀገሪቱን አንድ ክፍል ገንጥሏል። በመሆኑም ቀደም ሲል የተካሄደው የሙብትና የፍትሀዊ ኤኮኖሚ ትግል ባለፉት ሃያ አመታት በሀገር ማዳን ትግል ተተክቷል። የዚህ ሀገር የማዳኑም ተጋድሎ ዋነኛ ኢላማ ፀረ ኢትዮጵያዊ ዘረኝነት ሲሆን ሁኔታው ግድ እንደሚለው ይህ ትግል በታላቅ ኢትዮጵያዊ የአርበኝነት መንፈስ መመራቱ አማራጭ የሌለው ምርጫ ነው። ይህን ትግል ለማካሄድ የሚመሰረቱ ህብረትም ሆኑ ትብብሮች ኢትዮጵያዊነትን ያማከሉ እንዲሆኑ ግድ ነው። ማንኛውም በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል የሚመሰረት ትብብር የኢትዮጵያንና የህዝቧን አንድነት መሰረት ያደረገ እንጂ ይህን አንድነት ወደ ጎን የሚተውና ጥያቄም ውስጥ የሚከት ሊሆን በፍፁም አይችልም። ኢትዮጵያን ለማዳን ኢትዮጵያን ወደ ጎን መተው (አባንደን) ማድረግ ከቶም ትግል ሊባል አይበቃም።

የ ዶር ብርሃኑ መግለጫ በመሰረቱ አግላይና ፀረ ህብረት ነው። ምክንያቱም ከጅምሩ ኢትዮጵያውያን ሀይሎችን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን ራሱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቷልና። እንዳያማህ ጥራው መሆኑ ነው። ዶር ብርሃኑ ለኦነግ አይነቱ የጥላቻና የዘር ማጥፋት ወንጀለኞች ስብስብ የሰጡትን ሙብት(ኢትዮጵያዊነትን ቅድመ ሁኔታ ያለማድረግ) ኢትዮጵያን ለመሰለች ታላቅ ሀገርና ታላቅ ህዝብ ሲነፍጉ ማየት ከግምት በላይ ነው። ኦነግን ለማስደሰት ኢትዮጵያን ጭዳ ማድረግ። ነገሩ ግን የተልዕኮ ጉዳይ (ሚሽን) ነውና አንፈርድባቸውም።

እንደሚታወቀው ባሁኑ ወቅት ወያኔን እንታገላለን በሚሉ ሀይሎች መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት በወያኔ መውደቅ ላይ ሳይሆን ወያኔን በሚተካው ሥርአት ላይ ነው። ኦነግን ጨምሮ እንደ ስዬና ገብሩ አሥራትን አይነቶቹም በመለስ ያኮረፉ የህወሀት ዘረኞች የመለስን ከሥልጣን መወገድ ይሻሉ ይሁን እንጂ መለስን ማን ይተካው በሚለው ጥያቄ ላይ ያላቸው አቋም ከህዝባችን የኖረ ፍላጎት ጋር በእጅጉ የሚፃረር ነው። መሰረታዊውም ችግር የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው። የኦነግንም ሆነ የህወሀትን ዘረኞች የሚያመሳስላቸው ዘረኝነትን ዘላለማዊ ለማድረግ ያላቸው ህልም ነው። ሁለቱም ክፍሎች መለስ የሌለበትን ወያኔ ከነከፋፋይ ህገ መንግሥቱ ማስቀጠል ነው የሚፈልጉት። ወያኔን የምንታገለው በሌላ መሰል ዘረኛና ፀረ ኢትዮጵያ ሥርአት ለመተካት ከሆነ ከዝንጀሮ ቆንጆ መምረጥ ይሆናል። የወያኔን ሥርአት እንቃወማለን ሲባል ዘረኛ ሥርአትን ባጠቃላይ ማስወገድ ማለት እንጂ 'የተሻለውን' ሰይጣን ለሥልጣን ለማብቃት ከሆነ ትግላችን መርህ አልባ መሆኑን ጠቋሚ ብቻ ሳይሆን አንድን መከራ በሌላ ለመተካት የሚደረግን እኩይ አላማም አመላካች ነው።

የዶር ብርሃኑን የትብብር ቅድመ ሁኔታ በቅጡ ላስተዋለው ከዚህም ያለፈ መልእክት አለው። ይኸውም ኦነግ 'ተለወጠ' 'ኢትዮጵያዊም' ሆነ' ተብሎ በየስብሰባ አዳራሹና በየድረ ገፁ የሚነገረው ሁሉ ለፖለቲካ ፍጆታና አንድን ዘረኛ ሥርአት በመሰሉ ለመተካት በረጅሙ ለታሰበው ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮጄክት ለማመቻቸት ታስቦ የተፈበረከ ባዶ ውሸት መሆኑን ነው። እውን ኦነግ ፕሮግራሙን ከቀየረና ኢትዮጵያዊ ከሆነ ይህ ሁሉ የኢትዮጵያን አንድነት አሻፈረኝ ማለት ለምን ተፈለገ? ምን ለማትረፍ?

ከላይ በመግቢያው ላይ የተጠቀሰው በ 'አዲሱ' የኦነግ ፕሮግራም ላይ በ ቁጥር 1.3 ላይ እንደዋዛ ከሌሎች አንቀፆች መሀል የተደነቀረው አረፍተ ነገር የጠቅላላው ፕሮግራም አንዱ ክፍል ብቻ ሳይሆን የፕሮግራሙ መሰረትና የሁሉም አነጎች (የዳውድ፣የዲማ፣የገልቹ፣ የገለሳ፣ የኢብሳ...,) የወል ራዕይ ማጠንጠኛ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እንደገና መተርጎም በሪፈረንደም (ሪዲፋይን) ማድረግ ነው። ይህም በተግባራዊ መልኩ ሲገለጥ ህወሀት የጀመረውን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማፈራረስ ሂደት ማጠናቀቅ ይሆናል። የሁሉም አነጎች ህልም ከወያኔ ሥርአት መወገድ በኋላ በሚካሄድ ሪፈረንደም 'ኦሮሞ'' የተባለው ህዝብ (በምን መመዘኛ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ እንደሚለዩት ባይታወቅም) ጠመንጃ ተደግኖበት 'ኦሮሚያ ወይ ባርነት' የሚል የሻእቢያን ወንጀል በመድገም ኦነግ የሚጋልብባት 'ኦሮሚያን' መፍጠር ነው። በኦነግ አንጃዎች መሀል አለ የሚባለው ልዩነት ካለም ኢትዮጵያን በተመለከተ ወይም ከላይ የተጠቀሰውን የሪፈረንደም አቋም በተመለከተ አንድና አንድ ለመሆናቸው ቀጥሎ ያለው የኢብሳ ጉተማ (የሌላኛው ኦነግ ፕሮግራም አርቃቂ) ጥቅስ ምሥክር ናቸው።

***“Alliance with non- Oromo has first to be subject to referendum; otherwise, it could be taken as betrayal of the peoples cause.”***

ይህንኑ እኩይ አላማም ሻእቢያ ከጥንስሱ ጀምሮ (ሞቶ የተወለደ የተባለውን የመጀመሪያውን ኤ ኤፍ ዲ ጨምሮ) እስካሁን ድረስ እየተቆጣጠረውና እየመራው ለመሆኑ ሁለቱ ድርጅቶች (ግንቦትና ሁሉም የ ኦነግ አንጃዎች) ከሻእቢያ ጋር ያላቸው ቁርኝት ምሥክር ነው። በሻእቢያ የበላይ ተቆጣጣሪነት ከወያኔ ነፃ ለመውጣት የሚደረግ ትግል መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ጠቢብ መሆንን የሚጠይቅ አይደለም።

ኦነግ ከግንቦት ጋር ስምምነት የገባው እንደ አንድ የሌላ ሀገር ተወካይ እንጂ እንደ አንድ የተለየ የፖለቲካ ፕሮግራም (ፕላት ፎርም) እንዳለው ኢትዮጵያዊ ድርጅት አይደለም። ፕሮግራሙና በየስብሰባው የሚያውለበልበው ባንዲራው ይህንኑ ገላጭ ነው። ኦነግ ቀደም ብሎም ሆነ ‘አዲስ’ በሚለው ፕሮግራሙና በተለያዩ የፖሊሲ መግለጫዎቹ ግልፅ እንዳደረገው እንደ ስትራቴጂያዊ ግብና መሪ ዓላማ የሚታገልለት አንድነቷ በተጠበቀ ኢትዮጵያ ሥር እውን ለሚሆንና ሁሉን አሳታፊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ሳይሆን ለግዛት ጥያቄ ብሎም ለ ’ነፃነት’ ነው። የኦነግ ፕሮግራም አርቃቂ ኢብሳ ጉተማን ጥቅስ ያስታውሷል።

***“Neither democratized Ethiopia nor independent republic of oromiyaa will be realized unless the empire is dismantled”***

የኦነጎች ችግር ከፉ ሥርአቶች ሳይሆኑ ኢትዮጵያ ለመሆኗ ከላይ ከተጠቀሰው አባባል የተሻለ ማረጋገጫ ሊኖር አይችልም። የኢትዮጵያ መፈራረስ ኦነግ ለሚቃዥበት የ ኦሮሚያ ምሥረታ’ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ዶር ብርሃኑም ከላይ የተጠቀሰውን አንድነትን የሚኮንን ሀረግ በቅድመ ሁኔታነት ያስቀመጡት ይህንኑ ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮጄክት ለማመቻቸት ሲሆን ከ ‘አዲሱ’ የኦነግ ፕሮግራም ጋርም የተሰናሰለ (ሲንክሮናይዝድ) መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

የግንቦትና ደላሎቻቸው ኦነግ ‘ተለወጧል’ የሚለው ነጭ ውሸት ባዶ ማሞኛ ሲሆን አዲስና የተለወጠ ነገር ቢኖር ኦነግ በነ ዶር ብርሃኑ ግፊትና አሰልጣኝነት ከወትሮው በተለየ መልኩ ያልሆነውን መስሎ ለመቅረብ መሞከሩ ነው። ኦነግ ‘አዲስ’ እንዲሆን የተፈለገበትም ዋና ምሥጢር የዶር ብርሃኑ ግንቦት ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢዬ ነች ብሎ በግልፅ ከሚደሰኩረው ’አሮጌው’ ኦነግ ጋር የጀመረው ሤራ ታላቅ የህዝብ ተቃውሞ ስለገጠመው ሁለቱም ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች በዛ ሁኔታ ሊቀጥሉ ባለመቻላቸው በተለመደው የሻእቢያ መሰሪ ፖለቲካ ስልት የኦነግ ‘አንጃ’ እንዲፈጠርና ‘አዲስ’ አቋም እንዲይዝ ‘አሮጌውም’ ኦነግ ሴራውን እውነት ለማስመሰል ተቃውሞውን እንዲያሰማ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ድራማ ነው። አሁን አሁን ‘አሮጌውም’ ኦነግ እንደሚጠበቀው ‘ተቃውሞውን’ አቁሞ ድምፁን አጥፍቷል። በቅርቡም ባንድ የአሜሪካ ግዛት በተካሄደ ስብሰባ ላይ የ’አዲሱ’ ኦነግ ተወካይ ‘ካሮጌው’ ኦነግ ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት ተጠይቆ በቅርቡ ሁኔታዎች ተስተካክለው አንድ ላይ መስራት እንደሚጀምሩ ገልጿል የምሩን ነበር።

ሁላችንም እንደምናስታውሰው ዶር ብርሀኑ ‘ካሮጌው’ ኦነግ ጋር ይደራደሩ በነበረበት ወቅት አንድ ስብሰባ ላይ አስደሳች ሰበር ዜና ላብስራችሁ በማለት ‘ተለያይተው የነበሩት የኦነግ አንጃዎች አንድ ሆኑ’ ብለው በስብሰባው ላይ የተገኙ የማይጠይቁና የማይጠረጥሩ አድናቂዎቻቸውን እጃቸው እስኪቃጠልአስጨብጭበዋል። ያኔ ኦነግ ‘አዲስ ‘ ፕሮግራም አላወጣም ገና ‘አልተለወጠም’ ነበር። ዘንድሮ ደግሞ ኦነግ ‘ኢትዮጵያዊ ሆኗል፣ ተለውጧል’ አጨብጭቡ የጠፋው በግ ተገኝቷልና ሃሌ ሉያም በሉ እያሉን ነው። እድሜውን አይንፈገንና ይህን ሁሉ ጉድ እያስታወስን አንድ ቀን ነፃ በምትሆን ሀገራችን ባራዳ ልጆች አባባል እንደበርበታለን። ዶር ብርሃኑ የዘረኛው ኦነግ አንድ መሆንና መጠናከር ያስፈንድቃቸው እንጂ በተቃራኒው ለሀገር አንድነት ደፋ ቀና የሚሉትንና ለሳቸው ሀገር አውዳሚ ጉዞ እንቅፋት ናቸው የሚሏቸውን ኢትዮጵያውያን ድርጅቶችን ማየት እንደማይሹና መጠናከራቸውም እንደሚስፈራቸው ማስታወሱ እዚህ ላይ ስፍራው በመሆኑ የዛሬ አመት ገደማ ካስነበቡን መጣጥፍ ለአብነት ያህል ቀጥሎ እንመልከት።

“...በጠንካራ ድርጅቶች ከሚመራ የዲሞክራሲ የለውጥ እንቅስቃሴ ይልቅ ለራሳቸው ህይወት ሀላፊነት በወሰዱ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ዜጎችና በሺዎች በሚቆጠሩ የዜጎች ቡድኖች የሚመራ ትግል ለዲሞክራሲ ግንባታ ተመራጭና አስተማማኝ ነው። የህዝብ አቅም ሳይደረጅ የድርጅቶች አቅም ከሚገባው በላይ ማደግ ለህዝብ አደጋ ያረገዘ አካሄድ ነው...”

ቀጥሎ ባለው ሊንክ ገፅ 4 አንቀፅ ሁለት ([http://www.abbaymedia.com/Amharic/Civil- disob-Public.pdf](http://www.abbaymedia.com/Amharic/Civil-%20disob-Public.pdf) )

ዶር ብርሃኑ በ1998 የወያኔና ሻእቢያ ጦርነት ወቅት ሻቢያ መጥፋት ያለበት ቡድን ነው እስከማለት የደረሰ የወያኔ ደጋፊነታቸውን እንዳላሳዩ ሁሉ በቅርቡ ደግሞ የሻቢያ ተቆርቋሪ በመሆን የወያኔን ወረራ ለኢትዮጵያ በመስ|ጠት ‘ኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገር ኤርትራን ወረረች’ በማለት ከሻቢያም በላይ ሻቢያ ሆነው ኢትዮጵያን ለተባበሩት መንግሥታት እስከማሳጣት የደረሰ አቤቱታ አቅርበዋል። ባንድ ቅፅበት ሁለት ግቦች በራፍ ላይ መገኘት ይሏል ይህ ነው። ሥልጡን ፖለቲካ? ዶር ብርሃኑ ከሌሎች ፖለቲከኞች ለየት የሚያደርጋቸው አንድ ጉዳይ የኢትዮጵያን ፖለቲካ አስመልክቶ በተለያየ ወቅት በሚወስዱት አቋምና ውሳኔ የተጠያቂነት (አካውንተቢሊቲ) ስሜት የማይሰማቸው መሆኑ ሲሆን የፈለጉትን አቋም በፈለጉበት ጊዜ ለማራመድ የሚያስችል ለራሳቸው የሰጡት መብት (ኢንታይትልመንት) ያላቸው መሆኑ ነው። ሰውየው ተደምድሞ ያላበቃውና ህዝባችን ይሁንታ ያልሰጠውን የኤርትራን ሀገርነት በይፋ ሲያስተጋቡ ኤርትራን ዛሬ ድረስ እንደ ሀገሩ አካል የሚቆጥራትን ህዝባችንን ስሜት ምንኛ እንደሚያደሙት አላሰቡትም። ለህዝብ ሀገራዊ ስሜትና ቁጭት ደንታ የሌለው የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪ የፖለቲካን ሀሁ የመረዳት ችግሩን ብቻ ሳይሆን ለህዝብ ያለውንም ንቀት የሚያረጋግጥ ነው።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ሁለት አጥፊና ጠፊ ሀይሎች ተፋጠዋል። ኢትዮጵያዊነትና ፀረ ኢትዮጵያዊ ዘረኝነት። ፀረ ኢትዮጵያዊው ዘረኝነት በሁለት መልኩ የተገለጠ ሲሆን ባንድ በኩል ሥልጣን በጨበጠው የህወሀት ቡድንና ይህንኑ ቡድን ለመተካት በሚታገለውና በ’ተቃዋሚ’ ስም በሚንቀሳቀሰው የኦነግ ዘረኝነት በሌላ በኩል ናቸው። ስለሆነም ህዝባችን ህወሃት ወያኔን ሲታገል ኦነግና አዝማቹን ሻቢያን ላፍታም ቢሆን በመዘንጋት አይደለም። በመካሄድ ላይ ያለው ሀገር የማዳን ትግል ከመቼውም ጊዜ በላይ በጠንካራ ኢትዮጵያዊነት ስሜት መመራትን የግድ ይላል። ምክንያቱም ለጭፍን ፀረ- ኢትዮጵያዊነት ማርከሻው ጠንካራና ለድርድር የማይቀርብ ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነውና። የ ‘እሾኽን በሾኽ’ ምሳሌ ለዘረኝነት አይሰራም። ህዝብን አታጋዩ መፈክር (ሞቶ) ኢትዮጵያን ማዳን ሊሆን የግድ ይላል። የሩቁን ሆነ የቅርቡንም የሀገራችንን ታሪክ ብንመለከት ከኣድዋ እስከማይጨው እስከ ሶማሊያ እና በመካከሉ ያለፉትንም ጨምሮ በተካሄዱት ብሔራዊ ፍልሚያዎች ሁሉ በግንባር ተሰልፎ ውድ ህይወቱን ቤዛ አርጎ በደምና ባጥንቱ መስዋእትነት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል ያደረገው ገባሩና ድሃው ሰራተኛ ሲሆን በየዘመኑ በተነሱት አገዛዞች ቅጥ ላጣ የመብት ገፈፋና ኢሰብአዊ ለሆነ ጨካኝ ድህነት ተዳርጎ ኖሯል እየኖረም ነው። ይሁን እንጂ ህዝባችን እንደግለሰብም ሆነ እንደ ህ/ሰብ ከደረሰበትና እየደረሰበት ካለው ሰቆቃ የተነሳ የሀገሩን ህልውና የሚፈታተን አደጋ ሲደቀን ኢትዮጵያና ኢትዮያዊነትን ጥያቄ ውስጥ አላስገባም።ኢትዮጵያ ለኔ ምኔ ነች አላለም ። ኢትዮጵያ በሪፈረንደም ትፍረስም አላለም። ምክንያቱም የችግሮቹ ሁሉ ምንጭ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሳይሆኑ በየወቅቱ የተነሱት ክፉ ሥርአቶች መሆናቸውን ይገነዘባልና። ህዝባችን በታሪኩ ለምኒልክም ሆነ ለ አፄ ሀ/ስላሴ ስህተቶች ኢትዮጵያን ጉማ (የደም ካሳ) አድርጎ አላቀረበም። ከግል ህይወቱ የኑሮ ውጣ ውረድ ባሻገር ሁሌም የሀገሩን ደህንነት ያስቀድማልና።

ስለሆነም ኦነግ ብቸኛው ሰለባ ነኝና ኢትዮጵያ ትፍረስልኝ የሚለውን ጭፍን ጥላቻ የሚነዳው ምክንያት አልባ የበቀል ፍትወቱን ለማርካት ዶር ብርሃኑና የግንቦት ግብረ አበሮቻቸው ለርካሽና ሀላፊ የሥልጣን ፍርፋሪ ኢትዮጵያን በገፀ በረከትነት ለማቅረብ የሚያካሂዱትን ሀፍረተ ቢስ ዘመቻ ህዝባችን እንደወትሮው ሁሉ በተባበረ ትግሉ እንደሚያከሽፈውና በማያዳግም ሁኔታም አሳፋሪ ውድቀታቸውንን እንደሚያከናንባቸው ላፍታም አይጠረጠርም።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ህዝባችን በትግሉ የዘረኞችና የቅጥረኞችን ፀረ ኢትዮጵያ ሤራ ያከሽፋል።

ተሻለ ተስፋዬ